# እሪ በል ሥም አውጪ

ጊዜው ቅኝ ገዥነት የተጧጧፈበት ወቅት ነበር። መቼም ቅኝ ገዥዎች ባላገሩን ሕዝብ የዝቅተኝነት ስሜት እንዲሰማው ለማድረግና፣ እኛ የምንነግርህ እንጂ አንተ ያለህ እምነትና አስተሳሰብ ሁሉ ስህተት ነው ብለው ለማሳመን የማይፈነቅሉት ደንጊያ አልነበረም።ይህን መሰሉ የምራባዉያን መሠሪ ድርጊት ቅኝ በተገዙ ሕዝቦች ላይ ያስከተለዉ ሥነ-ልቡናዊና ማኅበራዊ ቀውስ ከ-እስከ አይባልም። በዚህ ሁኔታ የአፍሪካውያን ኑሮ በቅኝ ግዛት ሥር በነበረበት ወቅት የተፈፀመ አንድ ታሪካዊ ቀልድ ላጫውታችሁ ።

አንድ አዉሮፓዊ ቄስ አንዱን አፍሪካዊ በካቶሊክ ሃይማኖት ጠምቆ ስሙን ጆን ብሎ ካወጣለት በኋላ ፣ „ ጥሩ ካቶሊክ መሆን ከፈለግክ መዋሸት የለብህም፣ ደግሞ በዕለተ ዐርብ ጾም ስለሆነ ስጋ መብላት አይፈቀድልህም፡“ ብሎ አስጠንቅቆ በመምከር ወደ አገሩ ተመለሰ። ጆንም እንደተነገረው ጥሩ ካቶሊክ ለመሆን ጥረቱን ቀጠለ ። አይዋሽም፣ እንደተባለውም ይጾማል ። ከጊዜ በሁዋላ ግን ረሃብ ገባና ጆን ቤት ውስጥ ምግብ ጠፋ ። ቤተሰቡም ተቸገረ ። ጆን በእሱና በቤተሰቡ ላይ ረሃብ ሲጠና ጦሩን ይዞ ጫካ ወረደና አደን እያደነ ቤተሰቡን መቀለብ ጀመረ።

በዚህ መሃከል ቄሱ ከአዉሮፓ ይመለስና ለጉብኝት ወደ ጆን ቤት አቀና ። ጆን በጾም ቀን የጥንቸል ሥጋ ሲመገብ ደረሰበት ። „ጆን! ከአሁን ወዲያ ጥሩ ካቶሊክ አይደለህም፣ በጾም ቀን የተከለከለውን ሥጋ መብላት ጀምረሃልና;“ አለው ። ጆንም „ይህ ሥጋ አደይለም ዓሣ ነው“ ብሎ መለሰ። የካቶሊኩ ቄስ በዚህ ዓይን ያወጣ ክህደት ተናደደ ፣ጨሰ ። „እንዴት መብላትህ ሳያንስ ትዋሽኛለህ ? መዋሸት ጥሩ ካቶሊክ እንደማያደርግህ አታውቅም? „ ብሎ ጠየቀው። ጆን ሳቅ ብሎ „ አልዋሽሁም ይህ ጥንቸል አይደለም ዓሣ ነው „ብሎ ደረቀ።

የካቶሊኩ ቄስ በንዴት „ይህ እንዴት ዓሣ ይሆናል ?“ ብሎ ጆንን ጠየቀው ። ጆን በኩራት እንዲህ አለው ። „ትንሽ ውሃ አምጥቼ ረጨሁበት ። ከዚያም ካሁን ወዲያ አንተ ጥንቸል አደለህም ዓሣ ነህ አልኩትና ባረኩት ። ስለዚህም ዓሣ እንጂ ጥንቸል አይደለም ብሎ „ተከራከረ ። የካቶሊኩ ቄስ ይህንን አንተ ማድረግ አትችልም ። ሊሆንም አይችልም“ አለው። ጆን ፈርጠም ብሎ „‘ እንዴት አልችልም? አንተ እዚህ ሃገር ስትመጣ አቡኮ ነበርኩ ትንሽ ውሃ ረጭተህ አደለም እንዴ ጆን የሆንኩት?“ አለው ይባላል።

“አቡኮ“ ጆን እንደሆነዉ ሁሉ በልዩ ልዩ ምክንያት የተጸዉዖ ሥማችን እየተቀየረ መምጣት ከጀመረ ሰነበተ ። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ስሞቻችንን ወደ „ዘመናዊነት“ ለመቀየር የሚደረገው ሩጫ ከፍተኛ ሆኖአል ። በአንድ ወቅት የሚወለዱ ልጆች ስም ሁሉ የእንግሊዘኛ ቅላፄ ካልያዘ ሕፃኑ/ሕፃኗ በሞት የሚቀሰፍ/የምትቀሰፍ ይመስል፤ ሱዚ ፣ ቺቺ ፣ ቲቲ ፣ ፊፊ፣ ሚኪና ፣ጆኒ ወዘተ በዝቶ ነበር ።ዛሬ የወለድናቸውን ልጆች ድሮ በነበሩት ሥሞች መጥራት እንደ እንዳልሰለጠነ ሰው የሚያስቆጥረን የሚመስለን ብዙዎች ነን። የልጆቻችንን ሥም አስታውሶ ለመጥራት እስከሚያዳግተን ድረስ አዳዲስ ሥሞች ማውጣቱን ተያይዘነዋል ። የቅርብ ዘመዶችዎ ልጆች ሥም እየጠፋዎት በተውላጠ ወይም በቅጽል ሥም መጥራት የተገደዱበት ወቅት አጋጥሞት ያውቃል? ይህ በየዕለቱ በብዙዎቻችን ላይ የሚደርስ ነው።

ሥም በተለያየ ምክንያት ሕፃኑ ሲወለድ የነበረውን ታሪካዊና ቤተሰባዊ ሁኔታ ለማስታወስ ይወጣል። ለምሳሌ ከሃዘን በኋላ ማስረሻ ፣ ምትኬ፣ ባይልልኝ ፤ ደስታን ለመዘከር ደግሞ ደስታ ፣ፍስሃ ምስጋና ፣ወዘተ የሚል ስም መስጠት የተለመደ ነዉ። በባሕላችን የአባትና የልጅ ስም በቅንጅት ሲነበብ ትርጉም እንዲሰጥ ወይም እንደ ሰምና ወርቅ እንዲያገለግል ሆኖ ይወጣል። አንተነህ ንጉሡ ፣ ሰጥአድርጋቸው ዘላለም፣ ባገኘው ደስአለኝ . . . ወይም ደግሞ በዘመኑ መከፋትን ማጉረምረምን ለመግለፅ ፣ ድፉባቸው ፣

ደምመላሽ ፤. . . ወይም ዘመናዊ ወቅታዊ ሥሞች ፤እነ አልማዝ ፤ ውቢት፤ ቆንጂት ፤ ሃይማኖትን በሚመለከት ደግሞ ፤ እነ ወልደ ማርያም ፤ ገብረ እግዚአብሔር ሕፃኑ ወይም ሕፃኗ ለአምላክ ለቅዱሳን በአደራነት የተሰጠ ወይም የስዕለት ልጆች እንደሆኑ ለማሳየት ይሰጣሉ ። በአንዳንድ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ደግሞ አዲሱ ልጅ የሚወስደው ከመወለዱ ትንሽ ቀደም ብሎ ወደአካባቢዉ የመጣውን እንግዳ ስም ነው ።

በአፄ ሃይለስላሴ ዘመን በንጉሡ ነገስቱ መከፋታቸውን የሚገልፁ ስሞች እንደነበሩ የሚታወስ ነው ። ስሞችም ያሳስሩ እንደነበር ይነገራል ። ምን ያህል እውነተኛ እንደሆነ አላውቅም እንጂ ልጁን ይግባ ጎንደር ብሎ የሰየመ ዘውዱ የሚባል ሰው የስሙ ትርጉም ባመጣው መዘዝ የልጁን ስም አለውጥም ብሎ ታስሮ እንደነበር ሰምቻለሁ ። <<ይግባ ጎንደር ዘውዱ>> የሚለው ስም በወቅቱ እንደ የተቃውሞ ፖለቲካ ይቆጠር ስለ ነበር ነው። አጼ ሐይለሥላሤ መንግስቱ ነዋይ ሊገለብጣቸው አስቦ ሳይሳካለት ከቀረ በሁዋላ መንግሥቱ ኃይለማርያም ደግሞ በተራዉ እስር ቤት የወረወራቸዉ መሆኑን አስመልክተዉ ሲናገሩ ፤ “ካሁን በኋላ ወደ ስልጣን ተመልሰን ብንመጣ መንግሥቱ የሚባል ሰው በጦሩ ውስጥ አናስቀርም“ ብለው ቀልደው ነበር ይባላል።

ወቅትን ለማድነቅ / ለመምሰል ያህል የሚደረገው ጥረትም ለአስገራሚ ስሞች ብቅ ብቅ ማለት አንዱ ምክንያት ነው ። በአብዮቱ ወቅት የተወለዱ ልጆች መጠሪያቸዉ አብዮት፤መስከረም፤የካቲት ሆኖ ነበር ። አብዮት የሃገር እድገት ያመጣል ተብሎ ሰለተገመተ ግለሰቦች ልጆቻችውን አብዮት ብለው መጥራት የመረጡ ይመስላል።አብዮቱ ከጭፍጨፋ በቀር ያመጣው ፋይዳ እንደሌለ ሲታወቅ ደግሞ አብዮት የሚለው ሥም እየተጠላ መጣ ።ብዙዎቹ ከአብዮት ወደ አብነት ተለወጡ ። አብዮት ሲባል ይናደድ የነበረና በጋዜጣ ስሙን ያስቀየረ ግለሰብ አውቃለሁ ። አብዮት የሚለው ስም ያን የረሃብ ጊዜ ፤ የፋሽስቶችን ድርጊት ማስታወሻ እንጂ ፤ ሃገራችንን ከነበረችበት ችግር እንደተጠበቀው የሚያወጣ ሆኖ ሰላአልተገኘ ስሙ ራሱ ማፈሪያ ነበር የሆነው።

ለነገሩ አብዮት የመጣው ዐበየ ከሚለው የግዕዝ ቃል ነው።ዐበየ እንቢኝ አለ ዐመፀ ማለት ሲሆን ዐመፀኛው የሚለው ስም ምን ያህል ጥሩ ስም እንደሆነ ጥያቄዉን ለስም አውጭዎቹ እተወዋለሁ። ግን እነ ድፋባቸው ፤ በላቸው ፤ ግዛቸው የሚሉ ሥሞች ባሉበት ሃገር ዐመፀኛው የሚለው ሥያሜ ያን ያህል ላይከብድ ይችላል።አሁን ደግሞ እንደምንሰማው „ሕወሓት“ ፤ “ተገዳሊት“ ፤ “ ሐርነት“ የሚሉ ሰሞች የወያኔ መንግሥት በጠቀማቸው ሰዎች አካባቢ ብቅ ብቅ እያሉ ነው። የወያኔ መንግሥት በዘራቸው ምክንያት መከራ ያሳያቸዉ አቶ ዘገየ የተባሉ ግለሰብ ደግሞ ለልጃቸው ነፃነት የሚል ስም ሰላወጡ በወያኔ ካድሬዎች ከሥራ እንደተቀነሱ በቅርብ አንደ ወዳጄ አጫውቶኛል ።

ዘመን አለፈ። ትርጉም ካላቸው ስሞች አልፈን ምን ማለት እንደሆኑ እንኳን የማናውቃቸውን ስሞች ለልጆቻችን ማውጣት ያዝን ። ዛሬ ብዙ ስሞችን ስለማናውቃቸው የምንደነጋገረው እኛው ሆነናል ። የልጆቻችን ሥሞች እየጠፉን ነው ። እነ ጌታቸው ፤ እነ አበበ ፤ እነ ቆጭቶ፤ እነገመቹ ፤ እነ ዲለቦ ፤ እነ ሀጎስ ፤ እነ ከድር ፤ እነ አመሌ ሌሎችም የኢትዮጵያውያን ሰሞች እየተቀየሩ ነው ።

አዳዲሶቹ ሥሞች ከመፅሐፍ ቅዱስ ሰለሚወጡ የዕብራይስጥ ቋንቋ ትርጉም ያላቸው ሥም ሊሆኑ ይችላሉ ። ማን ያውቃል ሲተረጎሙ አበባ ፤አልማዝ፤ ከበደ ፤ ወርቂቱ፤ ገመቹ ፤ ቢነጋ ሊሆኑ ይችላሉ ። ከመፅሐፍ ቅዱስ ስያሜን መውሰድ ዓለም አቀፋዊ ባሕርይ አለው ብል ማጋነኔ አይደለም ። አዲስ ነገርም አይሆንም ።በተለይ ክርስትያን ኢትዮጵያውያን የመፅሐፍ ቅዱስ ስሞችን ከጥንት ጀምረን እንደምንጠቀም የታሪክ መፅሐፍቶች አበክረው ያስረዳሉ ። ግን የአሁኑ የስም አወጣጥ ጥራዝ ነጠቅ ከመሆኑ የተነሳ የጥንቶቹ ትርጉሙ ከባሕልና ከሃገር ወግ ጋር የማይዛመደዉን እየመረጡ እንዳልተውት አሁን በዘመናችን ብዙዎቻችን ለልጆቻችን የምናወጣው ስም ቅጥ ያጣ ሆኖአል። የምንፈልገው ሌላ ሰው ያልተጠቀመበት፡ ቀየር ያለ መሆኑን ብቻ ነው።

የዘመናዊነታችን መግለጫ፣ ሃይማኖታችንን ጠልቀን የማወቅ ምልክት እየመሰለን መራቀቅን የመረጥን ይመስላል ።

በዚህ ምክንያት አዳዲሶቹ ሥሞች ልዩ ናቸው ። የቅጠል ይሁኑ ፣ የሠይጣን ይሁኑ ፣ የብረት ይሁኑ ማንም የሚጠይቅ የለም ። ቢሆኑም ግድ የሚሰጠው ያለ አይመስልም። ብቻ "ልዩ" "አዲስ" ስም ይሁኑ ነው። ማንም ካልተጠቀመባቸው በልጆችችን ስም ልዩ መሆን አድናቆት ታቅፈን ለመቀመጥ ነው ሩጫው።ኬልቅያስ፣ አሞጽ፣ ኢዮሲያስ ፣ ኢዮሃቄም ፣ ኤዶማ ፣ ሲዶማ፣ አሞን ፣አበኔር ፣ረዓብ ፣ሄርማን ክርስቶስ የተቸነከረባቸው የምስማር ስሞች ሳይቀሩ ፣ (አዶር ፣አላዶር ፣ዳናት፣ አዴራ፣ ሮዳስ...) እነዚህ እንግዲህ የወቅቱ የመጠሪያ ሥሞች ናቸው ፡፡ ስለነዚህ ስሞች ወደ ፊት ጥናት ተደርጎ ሊቀመጥ ይገባል ። አልያ በስም መታወቅ ሊቀርና እሱ ፣ እሷ ፣ ቀዩ ፣ጥቁሩ ፣ ረጅሙ ፣ አጭሩ ፣ ታላቁ ፣ ታናሹ ብለን ልንደነጋገር ነው።

በጣም የሚገርመው ደግሞ ከወላጆቻችን የተሰጠንን ወጉን የጠበቀ ባሕላዊ - ሃገራዊ ስም ለዉጠን ለፈረንጅ አጠራር እንዲስማማ የምናደርገው ጥረት ነው ። ለምሳሌ <<ስንፈልግህ ተገኝ ወልደሚካኤል>> የሚባለው ግለሰብ ፣ የአባቱ ስም "ተገኝ" ወደ "ቲ" ይለወጥና ፣"ሚካኤልን" ይወስድና ያለ ምንም ማመንታት ስሜ " ቲ . ማይክ" ነው ብሎ ሲንጎማለል ይገኛል ።ይህ መሰሉን ተመልምሎ እርቃኑን የቀረ ትርጉም የለሽ ስም በፍርድ ቤት የሚስቀይሩ/ ያስቀየሩ ትንሽ አደሉም ።በተለይ የሌላ ሃገር ዜግነት ከተቀበሉ በኋላ ሥማቸው ማንነታቸውን ሊያጋልጥባቸው እንደሚችል ስለሚገምቱ ከዛች ደሃ ሀገር መፈጠራቸዉን ለመደበቅ ሲሉ ስማቸውን ያስቀየሩ እንዳሉ የሚታወቅ ነው ። ወደ ፈረንጆች ስም ለመጠጋት የምናደርገው ልምምድ የሚጀመረው በራሳችን ነው ። ስሞችቻን ሲመች ሙሉ በሙሉ ይቀየራሉ፡ ሳይመች ደግሞ ቅርንጫፉን ተመልምሎ ባዶውን እንደሚቀር ግንድ በጉንዱሽ ይቀራሉ ማለት ነው ። ይህ የተለመደ ነው ; "ኃይለ ማርያም" ቀርቶ "ማርያምን" ፣"እድሜአለም"ን ወደ "ኤዲ" ፣ "ሠናይት" ን ወደ "ሰኒ" ፣ "ተዋበች" ን ወደ "ታቢ" ፣ "ዓለሙ" ን ወደ "አሌክስ" ፣ ወዘተ ለመቀየር ሚደረገው ትግል ትንሽ አይደለም ። ታዲያ የገዛ ራሳችንን መጠሪያ ለመቀየር ጥረት የምናደርግ የልጆችችንን ስም ብንቀይር ምን ያስደንቃል ? ነገረ ሥራችን ሲታይ „ለፈረንጅ ምቾትና ደስታ መጠሪያቸዉን የሚሠዉ ብጹዐን ናቸዉ „ተብሎ የተጻፈ ይመስላል።

ወደ ጥንት ሥሞች እንመለስ ማለቱ ይከብድ ይሆናል።ስም በመጠኑም ቢሆን ወቅትን ማንፀበረቅ ይገባውም ይሆናል ። ቢሆንም ግን ትርጉማቸው የማይታወቅ ሥሞች ደግሞ ለምን እንደሚያስፈልጉ አይገባኝም ። በተለይ ከውጭ የምንዋሳቸው ስሞች ማንነታችንን በአሉታ ከማሳየት በቀር የሚያመጡት ለውጥ ይኖራል ብዬ አላምንም ። በስተርጅና ማይክ ካልተባልኩ ብሎ መታገል የሚያስገምት ነው። የሃገራችንን ሥሞች መያዝ ባሕላችንንና ቋንቋችንን ከትውልድ ወደ ትውልድ የማስተላለፍ አንዱ ተግባር መሆኑን መዘንጋት የለብንም ።

ስለ ሥም እኔ ልጀምረው እንጂ ብዙ ሊፃፍ ይችላል ። በተለይ ሊቃውንት ትምህርት ሊሰጡን ይገባል። መጤዎቹን ሥሞች ከነትርጉሞቻቸዉ ጋር እንድናዉቃቸው ቢደረግ ምን አልባት ከመሳሳት እንድን ይሆናል ።

ሰለኛ የሚያስብ በሰላም ይክረም

ይህንን ፅሁፍ በሚመለከት ሀሳብ መስጠት ለምትፈልጉ በዚህ ኢሜል አድራሻ ተጠቀሙ።
beljig.ali@gmail.com